# ዴሞክራሲያ

* የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን *

ዴሞክራሲያ ቅጽ 39 ቁ.3 ኅዳር/ታህሣስ 2006 ዓ.ም


## ያልተቋረጠ ትግል፤ ያልተቆጠበ መሥዋዕት

መሠረቱን በሕዝብ ፍቅርና በሀገር ጥቅም ላይ አድርጎ የሚታገል ድርጅት፣ ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ያልተቆጠበ ትግልና ያልተቆጠበ መሥዋዕት ከመክፈል የተለየ ባሕርይና ድርጊት አይኖረውም:: ትግሉን ሳያቋርጥ፣ መሥዋዕቱን ሳይቆጥብ፣ ለአምባገነኖች ሳይበገር፣ ለባላንጣዎቹ እጁን ሳይሰጥ፣ ለባዕዳን ኃይል ሳይንበረከክ፣ ኢትዮጵያዊ ብኩርናውን በጭብጥ ምስር ሳይለውጥ ለዘለዓለማዊት ኢትዮጵያ ዘለዓለማዊ ህልውና፣ ለዜጎቿም ዕኩልነት፣ አንድነትና ነፃነት መታገል፤ ክብር ብቻ ሳይሆን፣ ታላቅ ዕድለኝነት መሆኑንም ጭምር ይገነዘባል::

ስለዚህም እኮ ነው "ለኢትዮጵያ የሞትንላት አንድ ጊዜ ብቻ በመሆኑ ይቆጨናል !" በማለት የክብር ሞት የሞቱ ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ፍቅራቸውን የገለጹት! ይኸም ሀገራዊ ፍቅር እስከመቃብራቸው ብቻ ሳይሆን፣ ከኅልፈታቸው ባሻገር ጭምር መሆኑንም ያረጋግጣል:: አንድ ዜጋም ይሁን ድርጅት፣ ለሀገር ፍቅርና ለዜጎች ክብር የሚከፍለው የመጨረሻ ዋጋ የሕይወት መሥዋዕትነት በመሆኑ ሰማዕታቱ የመጨረሻውን ክብረ-ወሰን መጎናፀፋቸውን ማንም አይነሳቸውም:: በኢሕአፓ ትግል የተሰዉት ሰማዕታትም ማንነታቸውን የታሪክ ባለአደራ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሚገባ ያውቀዋል:: በአደራ ላይ የተመሠረተን ምስክርነት ለመስጠት ደግሞ ከኢትዮጵያ ሕዝብ የበለጠ የሞራል ልዕልና ሊኖረው የሚችል ሌላ ኃይል የለም ! የዛሬይቱ አገራችን ኢትዮጵያ፣ ላለፉት አርባ ዓመታት በተፈራረቁ የሦስት አምባገነን ሥርዓቶች ሰለባ ሆናለች:: ሦስቱም ሥርዓቶች፣ ለመንበረ-ሥልጣን አመጣጣቸው የተለያየ ምክንያትና አጋጣሚ ቢጠቀሙም፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጨቁኖ በመግዛት ግን ይህን ያህል ልዩነት አላሳዩም:: የጭቆናው አገዛዝ ውጤት የሆነው የሀገሪቱ ዕድል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋና እየተበላሸ ከመሄድ አልታገደም:: እንዲያውም በብዙ መልኩ እየተባባሰና ከድጡ ወደ ማጡ የሆነ አቅጣጫ ይዞ እየነጎደ ይገኛል::

ትላንት በአገሪቱ ከተሞችና የገጠር አካባቢዎች በአያሌ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጎች በግፍ ተጨፈጨፉ:: ዛሬ ግን የኢትዮጵያ ዜጎች የተጨፈጨፉት በሀገራቸው ብቻ ሳይሆን፣ በባዕድ ሀገራትም ጭምር ነው:: በየአደባባዩ፣ በአሰቃቂ ሁኔታ እየተጨፈጨፉ፣ በግፍ እየተደበደቡ፣ እየተንገላቱና እየተዋረዱ ናቸው:: ትላንትናና ከትላንት በስቲያ ሀገራችን በርሃብና በችጋር ምክንያት በዓለም ዙሪያ ትታወቅ እንደነበረው ሁሉ፣ ዛሬ ደግሞ ዜጎቿን በማሰደድና በባዕድ ሀገራት ተዋርደውና ተጎሳቁለው እንዲኖሩ በማድረግ በዓለም ቀደምት ቦታን ከያዙት ተርታ ነች:: ዛሬም ቢሆን ድህነትና ምፅዋት እየጠየቁ መኖር የኢትዮጵያውያን ልዩ መታወቂያ መሆኑ ቀጥሏል:: ትላንት ኅልቆ-መሳፍርት ዜጋ በእስር ቤት ሲማቅቅ እንደነበረ ሁሉ፣ ዛሬም ቁጥሩን በትክክል ለማወቅ ያልተቻለ ንፁህ ዜጋ፣ ሴት ወንድ፣ ወጣት ሽማግሌ፣ ምሁርና ባተሌ፣ ደራሲያንና

ጋዜጠኞች፣ ገጠሬና ከተሜ፣ የሃይማኖት አባቶችና ምዕመናን ሳይቀሩ፣ እንበለ-ፍርድ በዕስር ቤቶች እየማቀቁ ይገኛሉ፡፡

የትላንቶቹ አምባገነን ባለሥልጣናት፣ ከኋላ ቀር ባህል ከሚንፀባርቅ ልምድ በመነሳት፣ የፍርድ አድልዎ ለመፈፀም፣ ከደሃው ዜጋ ጉቦና መታያ የሚሆን፣ ማሰሮ ቅቤ፣ የዕርሻ ሰብል፣ ጠርሙስ አረቄ፣ የበግ ግልገልና የሰባ ሙክት ሲወስዱ እንደነበር ሁሉ፤ የዛሬዎቹ ደግሞ የሕዝብና የሀገር ሀብት በመዝረፍ ላይ ናቸው፡፡ ሙስናውና ዝርፊያው ከቁጥጥራቸው ውጭ የሆነው፣ የሕሊና ተገዥዎች ባለመሆናቸው ነው፡፡ በሚሊዮን ሳይሆን፣ በቢሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ ወደ ውጭ አገር ባንኮች በማሸሽ ላይ ይገኛሉ፡፡

ከስግብግብነትና ከሚያሳፍር ፍቅረ-ንዋይ ባህርያቸው የተነሳ፣ የደሃውን የዕለት መተዳደሪያ የሆነውን የጉልትና የችርቻሮ ንግዱን ሁሉ ሳይቀር እየተሻሙት ይገኛሉ፡፡ የፊውዳሉ ሥርዓትና የደርግ ባለሥልጣናት ንቀው የተውቱን የደሃውን ዝቅተኛ የንግድ መተዳደሪያ ሁሉ ሳይቀር የዛሬዎቹ ገብተው እየዋኙበት ነው፡፡ በዚህ ረገድ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሁለተኛ ዜጋ ደረጃ ተጠቃሚ የሚሆንበትን ዕድል ሁሉ እንኳን ሳይቀር ዘግተውበታል፡፡ ወያኔዎቹና ደጋፊዎቻቸው የሀገሪቱን ሁለንተናዊ የፖለቲካ፣ የምጣኔ ሀብት፣ የማኅበራዊና የንግድ እንቅስቃሴውን ሁሉ በመዳፋቸው ቀፍድደው በመያዝ እየበዘበዙ፤ ሌላው የበይ ተመልካች በመሆን የከፋ ኑሮውን ይገፋል፡፡ ይህ እኮ አልነበረም የየካቲት 66-ቱ አብዮት ዓላማና ግብ !

መሬት ላራሹ ለሚለው መሠረታዊ የሕዝብ ጥያቄ፣ ወያኔዎቹ፣ መሬት የመንግሥት ነው የሚል ምላሽ በመስጠት አዳፍነውታል፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ ከትላንቱ የፊውዳል ተጠማኝነት ለወያኔ ዘረኛ ሥርዓት ተገዥነት ተዳርጓል፡፡ ታሪካዊው የየካቲት 66 ሕዝባዊ አብዮት፣ መሬት ላራሹ ብሎ ያስተጋባው፣ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ዜጋ መሬትን በባለቤትነት የመያዝ መብትን እንዲጎናፀፍ ነበር እንጅ፣ ባዕዳን ዜጎችን የኢትዮጵያ መሬት ባለርስት ለማድረግ አልነበረም፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ የመከራ ገመዱ ያለመቆረጡ ብቻ ሳይሆን፣ ሀገሪቱ በታሪክ ዕንቆቅልሽ ውስጥ ገብታ የምትሽከረከር መሆኗን ያመለክታል፡፡ ሰፋፊና ለም መሬቶችን ለባዕዳን እየሸጠና እየለወጠ ባለ ሀብት እያደረገ፤ በአንፃሩ የሀገሪቱን ዜጎች በትውልድ አገራቸው በሊዝ አዋጅ ተጠማኞች ሆነው እንዲኖሩ ከማድረግስ የበለጠ ምን የታሪክ ምፀት ሊኖር ይችላል?

የኢትየጵያ አምባገነን ሥርዓት ከሌቹ አምባገነን ሥርዓቶች የከፋና የከረፋ፣ የጠነዛና የገለማ የሚያደርገው የራሱ መለያ አለው፡፡ ይኸውም፣ እህል ውሃው አልቆ ሲሄድ፣ ሀገሪቱን ማጥፋቱ ብቻ ሳይሆን ሰውም እንዳይኖራት አድርጎ መጥፋቱ ነው፡፡ ለዚኸም የዐፄውና የደርግ ሥርዓቶች በቂ ማስረጃዎች ናቸው፡፡ ወያኔም ከዚህ የተለየ ያደርጋል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ እጥፍቶ መጥፋትን እንጅ፣ እንደ ቀደምት ጀግኖች ኢትዮጵያውያን፣ ሀገር እድነን እንጥፋ አይሉም፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ እንከን-የለሽ የሀገር ፍቅርና ከጥያቄ ውስጥ የማይገባ ድፍረትና ለመሥዋዕት ዝግጁ መሆንን ይጠይቃል፡፡ የአምባገነን ነፈሰ-ገዳይነት የሚመነጨው፣ ከፍርሃትና ከመጨነቅ የተነሳ በመሆኑ፣ ተቃዋሚውን ሁሉ አጥፍቶ ከመጥፋት የተለየ ሌላ ምርጫ አይታየውም፡፡ የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ደግሞ፣ ሀገሪቱ ሰው አልባ መሆኗ ነው - የጀግና መጥፋት! ይኸም በበኩሉ "የተናቀ ሀገር በአህያ ይወረራል!" የሚል ተረት ያስተርታል፡፡ አንድን አዝመራ አንበጣ የሚወርረው እኮ፣ የአዝመራው ባለቤት የሆነው ገበሬ በአዝመራው አካባቢ አለመገኘቱ ነው፡፡ ለሀገር ተቆርቋሪና ለመሥዋዕት ቀራቢ የሆነ ትውልድ የሚፈጠረው ከአምባገነን ሥርዓት ሳይሆን ከጭቆናው ማኅፀን በመሆኑ፣ ዘረኛውን ሥርዓት ለመደምሰስ በሚደረገው የከተት ዓዋጅ፣ ላልተቋረጠው ትግልና

ላልተቆጠበው መሥዋዕት የተዘጋጀ ትውልድ እንደሚተካ ኢሕአፓ ብዥታ አይኖረውም። የአናብስት አገር የነበረችውም ኢትዮጵያ፣ የጀግኖች መፈንጫ ሆና አትቀርም። ይኸን አምኖ መታገል፣ ለትግሉ ወሳኝነት የበኩሉን አስተዋፅዖ ያደረጋል።

ያልተቋረጠውን ትግል እያካሄዱና ያልተቆጠበውንም መሥዋዕት እየከፈሉ መቀጠል አስፈላጊ የሆነው ዓብይ ጉዳይ፣ ትግልን ለመጀመር ምክንያት የነበሩት መሠረታዊ የሕዝብ ጥያቄዎች ምላሽ ባለመግኘታቸው ነው። የትግሉ ዓላማ መነሻና መድረሻ የሆኑት ዋናዎቹ ሀገራዊ ችግሮች እስካልተወገዱ ድረስ ደግሞ ትግል ማቋም የሚባል ጥያቄ አይኖርም። የኢትዮጵያ ችግሮች መፈታታቸው ቀርቶ እንዲያውም በአስጊና በአስከፊ ሁኔታ እየተባባሱ ናቸው። ይህ በሆነበት ሁኔታ፣ ትግልን ማቆም ማለት በትግሉ የተሰውቱን ሰማዕታት አደራ መብላት ብቻ ሳይሆን፣ ለሕዝብ የተገባለትን ብሔራዊ ቃል-ኪዳን እንደማፍርስ ይቆጠራል። በመሆኑም፣ ሕዝባዊ ጥያቄዎች እስካልተመለሱ ድረስ ትግሉን መቀጠሉ ለድርድር የሚቀርብ አይደለም።

የመጨረሻውን መሥዋዕት የሚጠይቀውን ትግል ለመቀጠል አስገዳጅ የሆነው ምክንያት፣ የሕዝብ ጥያቄዎች ባለመመለሳቸው ብቻም ሳይሆን፤ የሕዝብና የሀገር ችግሮች እንዲያውም እየተባባሱ በመሔዳቸውም ነው። በየካቲት 66 ዐብዮት የተነሱ ሕዝባዊ ጥያቄዎች አልተመለሱም ሲባል፤ እንዲያው ያለምክንያት በጭፍን የሚሰነዘር ነባቢት ሳይሆን ግዙፍ የሆኑትን ብሔራዊ ችግሮች በመገንዘብ ይሆናል። ዋና-ዋናዎቹን መመልከት ያስፈልጋል፡-

<u>የዴሞክራሲ መብቶች ያለገደብ ይለቀቁ</u>! ይህ ጥያቄ አሁንም በአንድ አምባገነን ሥርዓት መዳፍ ስርነው። የዴሞክራሲ ፀጋዎች፣ ማለትም በነፃ የመሰብሰብ፤ የመደራጀት፣ የመፃፍ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግና ጨቋኝ ሥርዓትን የመቃወምና ሃሳብንም ያለ ስጋት መግለጽ፣ ...ወዘተ ሁሉ እንደታፈኑ ናቸው። እነኝህን መሠረታዊ መብቶች የጠየቁ ሁሉ ያገኙት መልስ፣ ድብደባ፣ እስራትና ግድያ ብቻ ሆኗል።

<u>ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥት ይመሥረት</u>፡ ሕዝብ በነፃ ተደራጅቶ ገደብና ልኬታ በሌለው መብቶቹ ተጠቅሞ፣ የፈለገውን፣ የመረጠውን መንግሥት ማቋቋምና የሚስማሙትን መሪዎች መርጦ የመሰየም ጥያቄ የሕልም እንጀራ ሆኖ ቀርቷል። ከአንድ ብሔር የተውጣጡ ግለሰቦች ነፍጥ አንግበው በመምጣት፣ የራሳቸውን ብሔር የበላይነት ያሰፈነ አምባገነን ዘረኛ ሥርዓት አቋቁመው ቀሪውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨቁነው ይገዛሉ። ይህንን ዘረኛ ሥርዓት ቡራኬ ለመስጠት ሲሉም የወያኔን ድርጅት መተዳደሪያ ደንብና ሥርዓት፣ "የሀገሪቱ ሕገ-መንግሥት" ለማስመሰል በመጣር ገደብ-የለሽ ዘረኛ አምባገነን ሥርዓት አቋቁመው ሀገርን እያወደሙ፤ የሀገርን ሀብት እየዘረፉ፤ የዜጎችን ደብዛ እያጠፉ፤ ያሻቸውን እያደረጉ አሉ። የኢትዮጵያ ሕዝብም፣ "የምን ሕገ-መንግሥት? የማን ሕገ-መንግሥት?" እያለ ለወያኔ ሰነድ አመኔታና ክብር አልሰጠውም። የተፃፈበትን ወረቀት ያህል እንኳን ከበሬታ ስላልሰጠው፣ ሳይወድ በግድ ታፍኖ ተቀምጧል። ይህ የተዳፈነ እምቅ ኃይልና የታፈነው ድምፅ ተዋህዶ በመሚጣበት ጊዜ፣ የራሱን ሕገ-መንግሥት ቀርፆ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንደሚመሠረት የታሪክ ሐቅ ነው። እስከዚያው ድረስ ግን ያልተቋረጠውን ትግል እያካሄደና ያልተቆጠበውን መሥዋዕት እየከፈለ መታገሉን ይቀጥላል።

<u>መሬት ለአራሹ</u> ! ጭሰኛና ገባር፣ አስጠማኝና ተጠማኝ፣ በዝባዥና ተበዝባዥ ለሆነው ጉልታዊ አገዛዝ መሠረት የነበረውን የመሬት ስሪት ለውጦ፤ ለአብዛኛው የአገሪቱ ሕዝብ መተዳደሪያ የነበረውን የዕርሻ ክፍለ-ኢኮኖሚን ከሥር መሠረቱ መቀየር አስፈላጊ ነበር። በመሆኑም፣ የመሬት ለአራሹ ጥያቄ በየካቲት 66 ዐብዮት የተነሳው ዓይነተኛ ጥያቄ አሁንም ህያው እንደሆነ ነው። ሕዝብ መሬትን በባለቤትነት የመያዝ፤ የመውረስ-የማውረስ፤ የመሸጥ-የመለወጥ፤ በወለድ-አግድ መያዝና ማስያዝ ጥያቄ

እስካሁን ምላሽ አላገኘም:: ይልቁንም፣ የመሬት ይዞታ በአምባገነኖች ሥር እንዲሆን በሚደነግግ ሥርዓት ተተክቷል:: ሕዝብን የመሬት ባለቤት የሚያደርገውን ፖለቲካዊ፣ ሕጋዊና ኢኮኖሚያዊ መብትን ሽሮ፣ ሊዝ በሚል ፈሊጥ ተተክቶ፤ አምባገነኖች እንዳሻቸው የሚያዙበት-የሚናዝዙበት ሥርዓት ሰፍኗል:: ሕዝብ ተጠማኝና ገባር፣ መንግሥት አስጠማኝ በግድ አስገባሪ የሆነበት ሥርዓት ተንሰራፍቷል:: አስከፊውን የመሬት ይዞታ ለማሻሻል የተጠየቀው ሕዝባዊ ጥያቄ፣ "መሬት ለአራሹ" ነበር እንጅ መሬት ለመንግሥትና ለአምባገነኖች የሚል አልነበረም !

ወያኔ ይኸን ሥርዓት ያስረገጠው ያለ ምክንያት አይደለም:: ለራሱ የፖለቲካ ጠቀሜታና የኢኮኖሚ መገንቢያ ብልሀት ስላለው ነው:: ከፖለቲካው አኳያ የሥልጣን ዕድሜውን ለማራዘም በተለመው ዘዴ፣ ሕዝብን ከፋፍሎ፣ አደህይቶና አደንቁሮ፣ ታሪክን አዋርዶና ባህልን አርክሶ፣ ብሎም የተቃውሞ እንቅስቃሴውን ሁሉ ቅስም ለመስበር ይረዳኛል ብሎ ስለሚመኝ ነው::

አምባገነኖች የሚገዙትን ሕዝብ እንዳይቃወማቸው አስቀድሞ ቅስሙን መስበር የበለጠ ዘዴ ነው ብለው ያምናሉ:: ለዚህ ተስፋቸው ጊዚያዊ መፅናናትን ለማግኘት ሲሉም በመሣሪያ ኃይልና በፕሮፓጋንዳ ልፈፋ ይታጀባሉ:: ጊዚያዊ ዕፎይታ ያገኙ ሲመስላቸው የዕረኙም ጊዜ ሕልማቸው ዕውን እንደሆነ ይቆጥሩታል:: በጊዚያዊ መረጋጋት እየተፅናኑ፣ የማይቀረው መፃዒ የሕዝብ መነሳሳት መጥቶ እንደሚወገዱ እንኳን ለማሰብ ሕሌናቸው ይታወርባቸዋል:: "አለማወቅን አለማወቅ" የመጥፋት መጀመሪያ መሆኑን አለመገንዘብ፣ ጦሱ ለአድራጊው ብቻ ሳይሆን ለሀገርና ለሕዝብ ጭምር እንደሚተርፍ መገንዘብ ብልህነት ነው! ይህንን ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ከወያኔ መሪዎች አይጠብቅም::

<u>በሕዝብ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ የሚመጣ ፌደራላዊ ሥርዓት</u>:

ለቀልጣፋ አስተዳደር፣ በጊዜውና በቦታው ለሚወስን የፍትኅ-ርትዕ አሰጣጥ፣ ለተስተካከለ ልማታዊ ዕድገት የሚመች የፌዴራል ሥርዓት እንዲመሠረት የተጠየቀው ሕዝባዊ ጥያቄ በወያኔ ድርጅታዊ ሰንሰለት የተማከለ አሃዳዊ አገዛዝ ተጠርንፏል:: የወያኔን ባንዴራዎች የሚያውለበልቡ የጎሳ አገዛዞች ተኮልኩለዋል:: ከአንድ ፈላጭ ቆራጭ ጎሰኛ ፓርቲ የሚመነጭ ህግና ደንብ ትዕዛዝና አፈፃፀም የተቀነባበረ አሃዳዊ አገዛዝ ማለት ፌዴራላዊ አስተዳደር ማለት በጭራሽ አይደለም:: የአንድ ፓርቲ አምባገነንነት መንግሥት (ቶታሊታርያን) ሰንሰለት የተዋቀረ ያገዛዝ ሥርዓትን የዘረኝነት ቃና እየሰጡ የፌዴራል አስተዳደር አምጥተናል ማለት የፖለቲካ ሳይንስ ጠበብትን የትዝብት ፈገግታን ከማግኘት ያለፈ ዕርባና የለውም:: የወያኔ የጎሳ ፌደሬሽን፣ እጅግ የተጠናከረ የአንድ ፓርቲ (አሃዳዊ) አገዛዝ እንጅ የኢትዮጵያ ሕዝብ የጠየቀው ፌዴራላዊ አስተዳደር አይደለም:: ይህ የአንድ ብሔርን የበላይነት ለማስፍን ሲባል የተመሰረተ አገዛዝ፣ በሁሉም አቅጣጫ የሥልጣን መረቡን አንሰራፍቶና አጠንክሮ ይገኛል:: የአገዛዝ ማዕከላዊነቱም በዚያው መጠን ለአሃዳዊነቱ ማረጋገጫ ሆኗል:: የጦር ኃይሉ፣ የፖሊስ ሠራዊቱ፣ የፀጥታው መዋቅር (የደኅንነቱ ሰንሰለት)፣ የጉምሩክና የፊናንስ ድርጅቱ፣ በሙሉ የተማከለው የወያኔን አሃዳዊ አገዛዝ አደላድሎ ላልተወሰነ ጊዜ ኢትዮጵያን እየበዘበዙ፣ ሕዝቧንም እየጨቆኑ ለመግዛት በመሆኑ የየካቲት 66 ዐብዮት ሕዝባዊ ጥያቄን አልመለሰም:: በመሆኑም፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያነሳቸው አንኳር አንኳር ጥያቄዎች እስካልተመለሱ ድረስ ያልተቋረጠውን ትግል እየቀጠሉና ያልተቆጠበውን መስዋዕት እየከፈሉ ከመቀጠል ሌላ ምርጫ አይኖረንም !

በኢሕአፓ ዕምነት፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በደሉና ብሶቱ፣ ጭቆናውና ጥቃቱ እንደቀጠለ ነው፡፡ ይህም የሚፈፀምበት፣ በሀገር በውስጥ ባላንጣዎቹና በውጭ ጠላቶቹ ተባባሪነት ነው፡፡ የነኝህ ጠላቶች ትብብር ጥቃቱን አባብሶበታል፡፡ ይህም ሆኖ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈፅሞ አልተቸነፈም ! ሞራሉን አላስደፈረም ! መንፈሱን አላስነካም! ለባዕዳን ወራሪዎችና ለሀገር ውስጥ ተላላኪዎች አልተበገረም! ሕዝብ ደግሞ ምንም ምን ቢሆን ዝናሩን ፈትቶ ሊገብር ከቶ አይችልም፡፡ ለዚህ ጀግና ሕዝብ ከመታገል የበለጠ ደስታና ኩራት ስለማይኖር የሕዝቡ ሀገራዊ ጥያቄዎች ተገቢዉን መልስ እስኪያገኙ ድረስ፤ ያልተቋረጠውን ትግላችንን ያልተቋረጠው መሥዋዕታችን ጋር አዋህደን እንቀጥላለን !

ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!
ኢትዮጵያ በነፃነቷ ለዘለዓለም ትኖራለች!